ለምን ይገደሉ?

በአቡ ሀይደር

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በሆነው።

ምስጋና የዓለማት ጌታ ለሆነው ለአላህ የተገባ ነው። የአላህ ውዳሴና ሰላም፣ የሰላም አለቃና መምህር ለሆኑት ለነቢዩ ሙሐመድ ይሁን። ድልና የበላይነት ሐቅን ለማንገስና ሀሰትን ለማርከስ፣ በደልን አጥፎ ፍትህን ለማስፈን ዕውቀታቸውን፣ ንብረታቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ ጊዜያቸውንና ህይወታቸውን መስዋእት በማድረግ ለሚታገሉት ይሁን።

وَلَا تَقْتُلُوا النَّفْسَ الَّتِي حَرَّمَ اللَّهُ إِلَّا بِالْحَقِّ وَمَنْ قُتِلَ مَظْلُومًا فَقَدْ جَعَلْنَا لِوَلِيِّهِ سُلْطَانًا فَلَا يُسْرِفْ فِي الْقَتْلِ إِنَّهُ كَانَ مَنْصُورًا "سورة الإسراء 33

"ያቺንም አላህ ያወገዛትን ነፍስ ያለ ሕግ አትግደሉ፤ የተበደለም ሆኖ የተገደለ ሰው፣ ለዘመዱ (በገዳዩ ላይ) በእርግጥ ስልጣንን አድርገናል፤ በመግደልም ወሰንን አይለፍ፤ እርሱ የተረዳ ነውና።" (ሱረቱል ኢስራ 33)።

ትላንት በአላህ ፈቃድ፣ በኢስላም በሃይማኖት ማስገደድ የለም! በማለት፣ በተወሰነ መልኩ ቅዱስ ቁርአናዊ አንቀጾችን ተመልክተናል አልሐምዱ ሊላህ።

ዛሬ ደግሞ የምንመለከተው፡- በግድያ ዙሪያ የተነገሩ አንቀጾችንና፣ የጠላትን ከንቱ የማሳሳት ሙከራ በአላህ ፈቃድ እውነታውን በማብራራት ነው።

ክስ ቁጥር አንድ፡-

وَاقْتُلُوهُمْ حَيْثُ ثَقِفْتُمُوهُمْ وَأَخْرِجُوهُمْ مِنْ حَيْثُ أَخْرَجُوكُمْ وَالْفِتْنَةُ أَشَدُّ مِنَ الْقَتْلِ وَلَا تُقَاتِلُوهُمْ عِنْدَ الْمَسْجِدِ الْحَرَامِ حَتَّى يُقَاتِلُوكُمْ فِيهِ فَإِنْ قَاتَلُوكُمْ فَاقْتُلُوهُمْ كَذَلِكَ جَزَاءُ الْكَافِرِينَ "سورة البقرة 191

"ባገኛችኋቸውም ስፍራ ሁሉ ግደሉዋቸው። ከአወጧችሁም ስፍራ አውጧቸው፡ ፡ መከራም ከመግደል ይበልጥ የበረታች ናት። በተከበረው መስጊድም ዘንድ በርሱ ውስጥ እስከሚጋደሉዋችሁ ድረስ አትጋደሉዋቸው። ቢጋደሉዋችሁም ግደሉዋቸው፤ የከሓዲዎች ቅጣት እንደዚህ ነው።" (ሱረቱል በቀራህ 191)።

አንዱና ዋነኛው ክስ የማቅረቢያ ጥቅሳቸው ነው። አንቀጹ ስለነማን ያወራል? ለምን ይገደላሉ? መች ይገደላሉ? እስከምን ድረስ ነው ግድያው? አላማውስ

ምንድነው? የሚሉትን ነጥቦች ለማወቅም ሆነ ለመረዳት ዝግጁዎች አይደሉም። እነሱ ቶሎ ‹‹ወደ ገደለው›› በመግባት ብቻ ብዥታ ለመልቀቅ ነው። እውነታውን ማብራራት ደግሞ የኛ ግዳጅ ስለሆነ፣ ከዚህ ቀጥሎ ምላሹን እንከታተል።

መልስ፡-

የዚህን አንቀጽ ሙሉ ሀሳብ ለማግኘትና ለመረዳት፣ ከፊቱና ከኋላው ያሉትን ጥቅሶች መመልከቱ ወሳኝ ነው። ይህችን አንቀጽ ብቻ ቆንጥሮ ማውጣት ለራስ ተሳስቶ ሌላውንም ማሳሳት ይሆናል። በመሆኑም ከአንቀጽ 190 በመጀመር እንመልከተው፡-

" وَقَاتِلُوا فِي سَبِيلِ اللَّهِ الَّذِينَ يُقَاتِلُونَكُمْ وَلَا تَعْتَدُوا إِنَّ اللَّهَ لَا يُحِبُّ الْمُعْتَدِينَ
سورة البقرة 190

"እነዚያንም የሚጋደሉዋችሁን (ከሓዲዎች) በአላህ መንገድ ተጋደሉ። ወሰንንም አትለፉ፤ አላህ ወሰን አላፊዎችን አይወድምና።" (ሱረቱል በቀራህ 190)።

- ‹‹እነዚያንም የሚጋደሉዋችሁን (ከሓዲዎች)›› የሚለው፣ እነማንን ነው? ለሚለው ጥያቄ መልስ ነው። የአንቀጹ መልእክት እኛን ስለሚጋደሉ ሰዎች እንጂ፣ ሰላምን ፈልገው አርፈው የተቀመጡትን ወይንም ከኛ ጋር ጦር ላለመማዘዝ ቃል የተጋቡትን ሰዎች አይደለም። አንቀጹ በግልጽ ‹‹የሚጋደሉዋችሁን›› ሰዎች ነው ያለው። ታዲያ ምኑ ላይ ጥፋቱ? ሊጋደሉን የመጡ ሰዎችን አርፈን ቁጭ ብለን መጠበቅ አለብን? መስጂዶቻችንን ሲያፈራርሱ፣ ደማችንን ሲያፈሱ፣ ንብረታችንን ሲወርሱ፣ በሴቶቻችን ክብር ሲረማመዱ ተመልካች መሆን አለብን? መፍትሄው ግን፣ እኛም እነሱን መጋደል አለብን የሚለው ነው። ደግሞም አካሄዳችን እንዴት መሆን እንዳለበት ሲገልጽ፡-

- ‹‹በአላህ መንገድ ተጋደሉ›› ይላል። አዎ የመጋደሉ አላማ ይህ ነው። ለስሜታችን ወይም ለዘራችን ክብር ሳይሆን፣ በአላህ መንገድ መሆን አለበት። በአላህ መንገድ ሲባል፡- የአላህ ቃል የበላይ እስኪሆን፣ ፍትህ እስኪሰፍን እና በደል እስኪጠፋ፣ በሃይማኖታችን ሰበብ የሚደርስብን ጥቃት እስኪቆም ድረስ ማለት ነው። ከዛም በመቀጠል አንቀጹ፡-

- ‹‹ወሰንንም አትለፉ፤ አላህ ወሰን አላፊዎችን አይወድምና›› ይላል፡፡ የፍትህ ጥግ ማለት እንዲህ ነው፡፡ ‹‹ወሰንን አትለፉ›› የሚለው ኃይለ ቃል፡ አራት ነገሮችን በውስጡ ያቅፋል፡፡ እነሱም፡-

1. ያልተጋደሉንን ሰዎች መጋደል ወሰን ማለፍ ነው፡፡

2. ሰዎች መጋደሉን ሳይጀምሩ ቀድሞ መጀመሩም ወሰን ማለፍ ነው፡፡

3. የሚገደሉ ሰዎችን፡ ከመደበኛው ግድያ ውጪ የሰውነት አካልን መቆራረጥ በራሱ ወሰን ማለፍ ነው፡፡

4. በዚህ የመገዳደል ወቅት ላይ እንዳይነኩ የተከለከልናቸው ሰዎች አሉ፡፡ እነሱንም መግደል ወሰን ማለፍ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ሴቶችን፣ ህጻናትን፣ በእድሜ የገፉ አዛውንትን፣ ባህታውያንን፣ እንሰሳትን...በሙሉ፡፡ (ተፍሲር ኢብኑ ከሢር፡ ሱረቱል በቀራህ 190)፡፡

በተለይ ይህን ጉዳይ በተመለከተ ታላቁ ሶሐባ (የነቢዩ ባልደረባ) ዐብዱላህ ኢብኑ-ዐባስ (ረዲየላሁ ዐንሁማ) እንዲህ ይላል፡-

عن ابن عباس " :وقاتلوا في سبيل الله الذين يُقاتلونكم ولا تعتدوا إنّ الله لا يحب المعتدين " يقول :لا تقتلوا النساء ولا الصِّبيان ولا الشيخ الكبير وَلا منْ ألقى إليكم السَّلَمَ وكفَّ يَده، فإن فَعلتم هذا فقد اعتديتم .جامع البيان في تأويل محمد بن جرير الطبري : القرآن

"ሴቶችን፣ ህጻናትን፣ አዛውንትን፣ እጁን ከናንተ በመሰብሰብ ሰላምታን ያቀረበ ሰውን ሁሉ እንዳትገድሉ፡፡ ይህን ካረጋችሁ በርግጥም ወሰን አልፋችኋል" (ተፍሲሩ-ጠበሪይ፡ ሱረቱል በቀራህ 190፡ ቁ 3094)፡፡

በዚህ መልኩ ወሰን እንዳናልፍ ከከለከለን በኋላ አንቀጹን ሲዘጋው ‹‹አላህ ወሰን አላፊዎችን አይወድምና›› አለን፡፡ አላሁ አክበር!!

በዚህ መልኩ እኛን መጋደል ስለፈለጉ ሰዎች፡ የኛ አቋም ምን መሆን እንዳለበት ካብራራ በኋላ፡ ወደ ቀጣዩ አንቀጽ በመሄድ እነዚህን ወሰን ያለፉ አካላት እንዴትና የት እንደሚገደሉ አስረዳ፡፡ ቀጣዩ አንቀጽም እንዲህ ይላል፡-

وَاقْتُلُوهُمْ حَيْثُ ثَقِفْتُمُوهُمْ وَأَخْرِجُوهُمْ مِنْ حَيْثُ أَخْرَجُوكُمْ وَالْفِتْنَةُ أَشَدُّ مِنَ الْقَتْلِ وَلَا تُقَاتِلُوهُمْ عِنْدَ الْمَسْجِدِ الْحَرَامِ حَتَّى يُقَاتِلُوكُمْ فِيهِ فَإِنْ قَاتَلُوكُمْ فَاقْتُلُوهُمْ كَذَلِكَ جَزَاءُ الْكَافِرِينَ "سورة البقرة 191

"ባገኛችኋቸውም ስፍራ ሁሉ ግደሉዋቸው፡፡ ከአወጧችሁም ስፍራ አውጧቸው፡፡ መከራም ከመግደል ይበልጥ የበረታች ናት፡፡ በተከበረው መስጊድም ዘንድ በርሱ ውስጥ እስከሚጋደሉዋችሁ ድረስ አትጋደሉዋቸው፡፡ ቢጋደሉዋችሁም ግደሉዋቸው፤ የከሓዲዎች ቅጣት እንደዚህ ነው፡፡" (ሱረቱል በቀራህ 191)፡፡

- ‹‹ባገኛችኋቸውም ስፍራ ሁሉ ግደሉዋቸው›› በማለት፡ ልክ እነሱ እኛን በየትም ስፍራ ለመጋደል ቆርጠው እንደተነሱት፡ እናንተም ባገኛችኋቸው ስፍራ ግደሏቸው አለ፡፡ ደግሞም፡-

- ‹‹ከአወጧችሁም ስፍራ አውጧቸው›› በማለት፡ ከሀዲያን ሙስሊሞቹን (ሶሐቦቹን) ከመካ እንዳበረሯቸው፡ እነሱም እንዲያስወጧቸው ታዘዙ፡፡ ደግሞም የነሱ በአላህ ማጋራት፡-

- ‹‹መከራም ከመግደል ይበልጥ የበረታች ናት›› በማለት፡ የነሱ የጣኦት አምልኮ ተግባር ከሚደርስባቸው ግድያ በላይ የሆነ ጥፋት እንደሆነ ገለጸ፡፡ መከራ(በአላህ ማጋራት) ለአንድ ሰው ከሞት የከፋ ኃጢአት ነው፡፡ ስጋዊ ሞት ምድራዊ ቆይታን ያሳጥራል እንጂ፡ የመጨረሻውን ዓለም አያጠፋም፡፡ በአላህ ማጋራት ግን፡ ምንም እዚህ ምድር ላይ የኖሩትን ያህል ቢኖሩ፡ ነጌ መቋረጥ ለሌለው ዘላለማዊ ጀሀነም እሳት የሚዳርግ ጥፋት ነውና፡ የነሱ በመካ ውስጥ ጣኦት የማምለክ ኃጢአት (መከራ) ከሚደርስባቸው የነፍስ ግድያ አንጻር እጅግ የከፋ ድርጊት እንደሆነ ገለጸ፡፡ እንደዛም ሆኖ ደግሞ፡-

- ‹‹በተከበረው መስጊድም ዘንድ በርሱ ውስጥ እስከሚጋደሉዋችሁ ድረስ አትጋደሉዋቸው›› ይላል፡፡ የተከበረው መስጂድ ‹‹መስጁዱል ሐረም›› (የሙስሊሞች የሶላት ቂብላ) አላህ ዘንድ እንዲሁም ሙስሊሞች ዘንድ እጅግ የተከበረ ከመሆኑ የተነሳ፡ ጠላት ጦር አንስቶ እስኪጋደላቸው ድረስ እንዳይጋደሏቸው ታዘዙ፡፡ ጠላት ከጀመረ ግን፡-

- ‹‹ቢጋደሉዋችሁም ግደሉዋቸው፤ የከሓዲዎች ቅጣት እንደዚህ ነው›› በማለት፡ እነሱም አጸፋውን መመለስ እንዳለባቸው ተነገራቸው፡፡ ለከሀዲዎች የሚገባቸው ቋንቋ ይሄ ብቻና ብቻ ነው፡፡

ይህን አንቀጽ በዚህ ከቋጨ በኋላ በቀጣዩ ላይ ደግሞ እንዲህ ይላል፡-

فَإِنِ انْتَهَوْا فَإِنَّ اللَّهَ غَفُورٌ رَحِيمٌ "سورة البقرة 192 "

"ቢከለከሉም አላህ መሓሪ አዛኝ ነው።።" (ሱረቱል በቀራህ 192)።።

- ‹‹ቢከለከሉም›› የሚለው ቃል፡ ሁለት ትርጉሞችን ያቅፋል፡-

አንደኛ፡- እናንተን ከመጋደል ቢቆጠቡ ማለት ሲሆን፡ ያ ከሆነ ደግሞ እናንተም ተቆጠቡ፡ አትጋደሏቸው የሚል ይሆናል።።

ሁለተኛ፡- ከነበሩበት የጣኦት አምልኮ ታቅበው ወደ አላህ መንገድ በፈቃደኝነትና በተውበት ቢመለሱ የሚል ሲሆን፡ ያ ከሆነ ደግሞ ለዚህ ድርጊታቸው የሚገጥማቸው ምን እንደሆነ እዛው ላይ እንዲህ በማለት መልሱን ሰጣቸው፡- ‹‹አላህ መሓሪ አዛኝ ነው››።። የሰዎች ወንጀል የቱንም ያህል የበዛና የከፋ ቢሆንም፡ ከአላህ ራሕመት እና ምህረት ጋር ሊስተካከል አይችልም።። የሱ እዝነቱ ዓለሙን በሞላ ያካለለ ነውና (ሱረቱ ጋፊር 7)።

ከዚህ በኋላ የቀረው አንቀጽ ደግሞ፡- የዚህ የጦርነቱ የመጨረሻ ዓላማና ግብ እስከምን ድረስ ነው የሚለውን በማብራራት የሚቋጭ ነው።። እስኪ እንየው፡-

وَقَاتِلُوهُمْ حَتَّى لَا تَكُونَ فِتْنَةٌ وَيَكُونَ الدِّينُ لِلَّهِ فَإِنِ انْتَهَوْا فَلَا عُدْوَانَ إِلَّا عَلَى الظَّالِمِينَ "سورة البقرة 193

"ሁከት እስከማይገኝና ሃይማኖት ለአላህ ብቻ እስከሚኾን ድረስ ተጋደሉዋቸው፡ ፡ ቢከለክሉም ወሰንን ማለፍ፤ በበዳዮች ላይ እንጂ የለም (ወሰን አትለፉባቸው)፡ ፡" (ሱረቱል በቀራህ 193)።።

- ‹‹ ሁከት እስከማይገኝና ሃይማኖት ለአላህ ብቻ እስከሚኾን ድረስ ተጋደሉዋቸው›› የሚለው የመጨረሻን ግብ የሚገልጽ ነው።። የኛ ዓላማ መሆን ያለበት፡ የሰው ዘር እንዲጠፋ፣ ወይም ብሄርተኝነት እንዲስፋፋ ሳይሆን፡ የአላህ ዲን የበላይ እንዲሆን ነው።። የጣኦት አምልኮ ተንኮታኩቶ፡ እውነትም ነግሶ በምድር ላይ እንዲታይ፡ አማኞችም ጌታቸውን የማምለክ ነጻነታቸው ተጠብቆ እንዲቆይ ነው።። ጠላት እንዳይበታትነን ሁሌም በንቃት መስራት ይጠበቅብናል፡ ፡

- ‹‹ሃይማኖት ለአላህ ብቻ እስከሚኾን ድረስ ›› ማለትም ትርጉሙ ይኸው ነው፡ ፡ የአላህ ሸሪዓ በምድር ላይ ነግሶ፡ የሰዎች ነጻነት ታውጆ፡ የኩፍር የበላይነት አክትሞ እስኪንኮታኮት ድረስ ማለት ነው።።

አንዳንድ ወገኖች፡- ሰዎች ሁሉ እስኪሰለሙ ድረስ ለማለት ነው ይሉናል።። እነሱ እንደሚሉት ከሆነማ፡- ‹‹ሃይማኖት ለአላህ ብቻ እስከሚኾን ድረስ›› ከማለት

ይልቅ፡ ‹‹ሰዎች ሁሉ ሃይማኖተኛ እስኪሆኑ ድረስ›› አይልም ነበር ታዲያ? ከየት ያመጣችሁት ግንዛቤ ነው? እንደውም ቀጣዩ ቃል ይህን ሃሳብ ያፈርስባችኋል፡፡

- ‹‹ቢከለክሉም›› የሚለው ሁለት ትርጉምን ያቅፋል፡፡

አንደኛ፡- ከዚህ ካሉበት የጣኦት አምልኮ ተከልክለው ኢስላምን በፈቃደኝነት ቢቀበሉ የሚል ሲሆን፡

ሁለተኛው፡- በነበሩበት የክህደት እምነት መዘውተርን ፈልገው፡ ኢስላምን ባይመርጡና ነገር ግን ለሚያስተዳድረው ኢስላማዊ መንግስት ያለባቸውን ‹‹ግብር›› በአግባቡ ቢከፍሉ የሚል ሲሆን፡ ከሁለት አንዱን ቢተገብሩ ውጤቱ ደግሞ፡-

- ‹‹ ወሰንን ማለፍ፤ በበዳዮች ላይ እንጂ የለም (ወሰን አትለፉባቸው)›› በማለት፡ በነሱ ላይ ወሰን ማለፍን ይከለክላል፡፡ (ተፍሲር ቁርጡቢይ፡ ጀሚዑል አሕካም)፡ ፡

እንደሰዎቹ ግንዛቤ፡ ሙስሊም እስኪሆኑ ድረስ ከተባለማ፡ ካልሰለሙ ግደሏቸው እንጂ፡ ወሰን አትለፉባቸው እንዴት ይባላል? ስለዚህ ‹‹ሃይማኖትም ለአላህ እስኪሆን ድረስ›› ማለት፡- ሰዎች ያለ ፈቃዳቸው አምነው እስኪቀበሉ ማለት አይደለም፡፡ ትላንት በጉዳዩ ላይ በመጠኑ ተመልክተነዋል)፡፡

ነገር ግን መልእክቱ፡- ፈቅደውና ወደው ኢስላምን እስኪቀበሉ፡ ያ ካልሆነም ለኢስላማዊው መንግስት የሚጣልባቸውን ግብር እስኪከፍሉ ድረስ ነው የሚለውን ያቀፈ ነው፡፡

ወንድምና እህቶች ከቁጥር 190-193 ያለውን የቅዱስ ቁርኣን አንቀጽ በመጠኑም ቢሆን እንዲህ ከተረዳነው፡ ታዲያ የታለ ሰዎች እስኪሰልሙ ድረስ ግደሏቸው የሚለው? የታለ ከመሬት ተነስታቹ ሰው አጥፉ የሚለው? መልሱን ለህሊና፡፡ ወላሁ አዕለም፡፡

ሌሎች አንቀጾችን ደግሞ እንዳይረዝምባችሁ በማለት እዚህ ላይ ማቆሙን ስለ መረጥኩ፡ በቀጣዩ ደግሞ ቀሪዎቹ ላይ በአላህ ፈቃድ እመለስበታለሁ፡፡ ነገር ግን ከመጽሀፍ ቅዱስ አንድ ጥቅስ ጠቅሼ ልለያችሁ፡፡ እንዲህ ይላል፡-

‹‹እግዚአብሔርም፡- በከተማይቱ በኢየሩሳሌም መካከል እለፍ፥ በመካከልዋም ስለ ተሠራው ርኵሰት ሁሉ በሚያለቅሱና በሚተክዙ ሰዎች ግምባር ላይ ምልክት ጻፍ አለው። እኔም እየሰማሁ ለሌሎቹ፡- እርሱን ተከትላችሁ በከተማይቱ መካከል እለፉ ግደሉም፤ ዓይናችሁ አይራራ አትዘኑም፤ሽማግሌውንና ጐበዙን

ቄንጆይቱንም ሕፃናቶቹንና ሴቶቹን ፈጽማችሁ ግደሉ፤ ነገር ግን ምልክቱ ወዳለበት ሰው ሁሉ አትቅረቡ፤ በመቅደሴም ጀምሩ አላቸው። በቤቱም አንጻር ባሉ ሽማግሌዎች ጀመሩ። እርሱም። ቤቱን አርክሱ፥ በተገደሉትም ሰዎች አደባባዮችን ሙሉ፤ ውጡ አላቸው። እነርሱም ወጥተው በከተማይቱ ገደሉ።›› (ትንቢተ ሕዝቅኤል ምዕ9 ቁ4-7)።

وَلَا تَقْتُلُوا النَّفْسَ الَّتِي حَرَّمَ اللَّهُ إِلَّا بِالْحَقِّ وَمَنْ قُتِلَ مَظْلُومًا فَقَدْ جَعَلْنَا لِوَلِيِّهِ سُلْطَانًا فَلَا يُسْرِفْ فِي الْقَتْلِ إِنَّهُ كَانَ مَنْصُورًا "سورة الإسراء 33

"ያቺንም አላህ ያወገዛትን ነፍስ ያለ ሕግ አትግደሉ፤ የተበደለም ሆኖ የተገደለ ሰው፣ ለዘመዱ (በገዳዩ ላይ) በእርግጥ ስልጣንን አድርገናል፤ በመግደልም ወሰንን አይለፍ፤ እርሱ የተረዳ ነውና።" (ሱረቱል ኢስራእ 33)።

ክስ ቁጥር ሁለት፡-

فَلْيُقَاتِلْ فِي سَبِيلِ اللَّهِ الَّذِينَ يَشْرُونَ الْحَيَاةَ الدُّنْيَا بِالْآخِرَةِ وَمَنْ يُقَاتِلْ فِي سَبِيلِ اللَّهِ فَيُقْتَلْ أَوْ يَغْلِبْ فَسَوْفَ نُؤْتِيهِ أَجْرًا عَظِيمًا "سورة النساء 74

"እነዚያም ቅርቢን ሕይወት በመጨረሻዪቱ ሕይወት የሚለውጡ፣ በአላህ መንገድ ይጋደሉ፤ በአላህም መንገድ የሚጋደል፣ የሚገደልም፣ ወይም የሚያሸንፍ፣ ታላቅ ምንዳን በእርግጥ እንሰጠዋለን።" (ሱረቱ-ኒሳእ 74)።

በዚህ አንቀጽም ላይ ያቀረቡት ክስ ተመሳሳይ ነው። አሁንም ቅዱስ ቁርአን ሰዎችን ግደሉ ይላል በማለት ያንኑ ካላወቀ አእምሮ የፈለቀ ትችታቸውን ይሰነዝራሉ።

ምላሽ፡-

የአንቀጹን ሙሉ ሀሳብ ለማግኘት ከኋው ያሉትን ሁለት አንቀጾች እንመለከታቸዋለን። ከዛ በፊት ግን የዚህን አንቀጽ ሙሉ ሀሳብ እንየው፡-

የመጨረሻውን ዓለም (የጀነትን ህይወት) በመፈለግ፡ ምድራዊ ህይወታቸውን መስዋእት አድርገው የሚለውጡ ሰዎች አማኞች ናቸው። እነዚህ አማኞች በአላህ መንገድ ጠላትን በመጋደል፡ ህይወታቸውን እንኳ መስዋእት ለማድረግ ወደ ኋላ አይሉም። ስለዚህም በአላህ መንገድ ጠላትን ሲጋደሉ፡ ድል ቀንቷቸው ቢያሸንፉም፡ ወይንም ተሸንፈው ቢገደሉም (ሸሂድ ቢሆኑ) አላህ በመጨረሻው ዓለም መልካም ስጦታን (ጀነትን) አዘጋጅቶላቸዋል። ምክንያቱም የተጋደሉት በሱ መንገድ ነውና። ያለ አግባብ የሰው ደም አላፈሰሱም። ከመሬት ተነስተው ረብሻ

አልፈጠሩም፡፡ ለዘራቸው ክብር አልተዋጉም፡፡ የተዋጉት በአላህ መንገድ፡ የአላህን ቃል የበላይ ለማድረግ፡ በአቅመ ደካማ አማኞች ላይ የሚደርስን የጠላት አደጋና ስቃይ ለማስቆምና ለመግታት ብቻና ብቻ ነው፡፡ ቀጣዩ አንቀጽም የነዚህን ጠላትን የመጋደልን ምክንያት እንዲህ ያብራራዋል፡-

وَمَا لَكُمْ لَا تُقَاتِلُونَ فِي سَبِيلِ اللَّهِ وَالْمُسْتَضْعَفِينَ مِنَ الرِّجَالِ وَالنِّسَاءِ وَالْوِلْدَانِ الَّذِينَ يَقُولُونَ رَبَّنَا أَخْرِجْنَا مِنْ هَذِهِ الْقَرْيَةِ الظَّالِمِ أَهْلُهَا وَاجْعَلْ لَنَا مِنْ لَدُنْكَ وَلِيًّا وَاجْعَلْ لَنَا مِنْ لَدُنْكَ نَصِيرًا "سورة النساء 75

"በአላህ መንገድና፤ ከወንዶች፤ ከሴቶችና ከልጆችም የኾኑትን ደካሞች እነዚያን፡- ጌታችን ሆይ! ከዚች፤ ባለቤቶችዋ፤ በዳይ ከኾኑት ከተማ አውጣን፤ ከአንተም ዘንድ ለኛ፤ አሳዳሪ አድርግልን ከአንተ ዘንድም ለኛ ረዳትን አድርግልን የሚሉትን (ለማዳን) የማትጋደሉት፤ ለእናንተ ምን አላችሁ?" (ሱረቱ-ኒሳእ 75)፡፡

በዚህ አንቀጽ ላይ በግልጽ እንደምናየው፡- ከወንዶች፤ ከሴቶችና ከልጆች የሆኑ አቅመ ደካሞች፡ በጠላት ተማርከውና ተበድለው ሳለ፡ እነሱም፡- ጌታችን ሆይ ከነዚህ በዳይ ከሆኑት ህዝቦች ከተማ (መካ) በሰላም አውጣን፡ ለኛም ረዳትና አሳዳሪን አምጣልን እያሉ እየተማጸኑ፡ ታዲያ አማኞች ካልታገሉላቸው፡ ጠላትን መከተው እነሱን ካላተረፏቸው ምኑ ላይ ነው የእምነት ትርጉሙ? ወይንስ ከዳር ቆመው በትዝብት ማየት ብቻ ነው የሚጠበቅባቸው? ወገኖች ምን ሆናችኋል? በምንስ አእምሮ ነው የምታስቡት? እራስን ሆነ ሌላውን ወንድም ከአደጋና ከጠላት መከላከል እኮ አምላካዊም ህገ መንግስታዊም መብት ነው፡፡ ህሊናስ አይቀበለውምን? ከዚህ በኋላ ነው እንግዲህ እነዚህን በዳይ ህዝቦች፡ የሰይጣን ሰራዊትን እንዲጋደሏቸው አላህ እንዲህ ያላቸው፡-

الَّذِينَ آمَنُوا يُقَاتِلُونَ فِي سَبِيلِ اللَّهِ وَالَّذِينَ كَفَرُوا يُقَاتِلُونَ فِي سَبِيلِ الطَّاغُوتِ فَقَاتِلُوا أَوْلِيَاءَ الشَّيْطَانِ إِنَّ كَيْدَ الشَّيْطَانِ كَانَ ضَعِيفًا "سورة النساء 76

"እነዚያ ያመኑት ሰዎች፤ በአላህ መንገድ ይጋደላሉ፤ እነዛ የካዱትም በጣዖት መንገድ ይጋደላሉ፤ የሰይጣንንም ጭፍሮች ተጋደሉ። የሰይጣን ተንኮል ደካማ ነውና።" (ሱረቱ-ኒሳእ 76)፡፡

እነዚህን የሰይጣን ጭፍሮች ነው እንድንጋደላቸው የታዘዝነው እንጂ፡ ሰላም ፈላጊዎችን፡ ንጹሀን ህዝቦችን አይደለም፡፡ ታዲያ ይህን ጥቅስ ለክስ ያቀረባችሁ

ወገኖች፡ ለሰይጣን ጭፍሮች ጥብቅና እየቆማችሁ ነው ማለት ነው? አማኞችን ሲያንገላቱና ሲያስሩ፡ ማርከውም ሲያሰቃዩ ዝም በሉ እያላችሁን ነው? ተዉ እንጂ ትንሽ አስቡ፡፡ ለመብት መታገል ሰብአዊነት ሲሆን፡ በደልን እያዩ በመቃወም ፈንታ በዝምታ ማለፉ ደግሞ ኢ-ሰብአዊነት ነው፡፡

ክስ ቁጥር ሶስት፡-

وَدُّوا لَوْ تَكْفُرُونَ كَمَا كَفَرُوا فَتَكُونُونَ سَوَاءً فَلَا تَتَّخِذُوا مِنْهُمْ أَوْلِيَاءَ حَتَّى يُهَاجِرُوا فِي سَبِيلِ اللَّهِ فَإِنْ تَوَلَّوْا فَخُذُوهُمْ وَاقْتُلُوهُمْ حَيْثُ وَجَدْتُمُوهُمْ وَلَا تَتَّخِذُوا مِنْهُمْ وَلِيًّا وَلَا نَصِيرًا "سورة النساء 89

"(እነሱ) እንደካዱ ብትክዱና እኩል ብትሆኑ ተመኙ! በአላህም ሃይማኖት እስከሚሰደዱ ድረስ ከነሱ ወዳጆችን አትያዙ፤ (ከእምነት) ቢያፈገፍጉም ያዙዋቸው፤ (ማርኩዋቸው) ባገኛችሁበትም ስፍራ ግደሉዋቸው፤ ከነሱም ወዳጅንና ረዳትን አትያዙ።" (ሱረቱ-ኒሳእ 89)፡፡

እዚህም ላይ የተለመደ ክሳቸውን አቅርበዋል፡፡ ወደ ገደለው በመግባት ‹‹ባገኛችሁበትም ስፍራ ግደሉዋቸው›› የሚለውን ብቻ ቆንጥሮ በማውጣት ብዥታ ለመፍጠር ይሞክራሉ፡፡ የአንቀጹን ትክክለኛ ፍቺ ለማወቅ አንድ አንቀጽ ከፊቱ በማስቀደም፡ አንድ አንቀጽ ደገሞ ከኋላው በማስከተል ለማብራራት እሞክራለሁ፡፡

فَمَا لَكُمْ فِي الْمُنَافِقِينَ فِئَتَيْنِ وَاللَّهُ أَرْكَسَهُمْ بِمَا كَسَبُوا أَتُرِيدُونَ أَنْ تَهْدُوا مَنْ أَضَلَّ اللَّهُ وَمَنْ يُضْلِلِ اللَّهُ فَلَنْ تَجِدَ لَهُ سَبِيلًا "سورة النساء 88

"በመናፍቃንም (ነገር) አላህ በስራዎቻቸው ወዋስትና እንዴት ተጠብቆ ሊቆይ ይችላል? እንዴትስ ትውልድና ማኅበረሰብ እንዲሁም ዘር ቀጣይነት ሊኖረው ይችላል?

ለሱማ ምድራዊ መንግስታት አሉ አይደል እንዴ? የምትሉ ከሆነ፡ ያ ለናንተ ያስፈለገበት ምክንያት፡ በምድራዊ መንግስታት ምትክ ቦታውን በመሸፈን ህዝብንና ሀገርን የሚመራና የሚያስተዳድር መመሪያ ስለሌላችሁ ነው፡፡ ፍትሐ ብሄር እና ወንጀለኛ መቅጫ ህግ የሌለው አካል ምድራዊ ስርአትን ከመደገፍ ውጪ አማራጭ የለውም፡፡ ኢስላም ግን አይደለም ሀገርን ዓለምን ማስተዳደር የሚችል መንፈሳዊና ስጋዊ መመሪያዎችን ሁሉ ያቀፈ ህግ አለው፡፡ ሙስሊም

አድርጎ ለፈጠረን፣ እስካሁንም በጸጋው በሙስሊምነት ላቆየን ጌታ አላህ ምስጋና ይገባው።።

وَلَا تَقْتُلُوا النَّفْسَ الَّتِي حَرَّمَ اللَّهُ إِلَّا بِالْحَقِّ وَمَنْ قُتِلَ مَظْلُومًا فَقَدْ جَعَلْنَا لِوَلِيِّهِ سُلْطَانًا فَلَا يُسْرِفْ فِي الْقَتْلِ إِنَّهُ كَانَ مَنْصُورًا "سورة الإسراء 33

"ያቺንም አላህ ያወገዛትን ነፍስ ያለ ሕግ አትግደሉ፤ የተበደለም ሆኖ የተገደለ ሰው፣ ለዘመዱ (በገዳዩ ላይ) በእርግጥ ስልጣንን አድርገናል፤ በመግደልም ወሰንን አይለፍ፤ እርሱ የተረዳ ነውና።" (ሱረቱል ኢስራእ 33)።።

ክስ ቁጥር አምስት፡-

قَاتِلُوا الَّذِينَ لَا يُؤْمِنُونَ بِاللَّهِ وَلَا بِالْيَوْمِ الْآخِرِ وَلَا يُحَرِّمُونَ مَا حَرَّمَ اللَّهُ وَرَسُولُهُ وَلَا يَدِينُونَ دِينَ الْحَقِّ مِنَ الَّذِينَ أُوتُوا الْكِتَابَ حَتَّى يُعْطُوا الْجِزْيَةَ عَنْ يَدٍ وَهُمْ صَاغِرُونَ "سورة التوبة 29

"ከነዚያ መጽሐፍን ከተሰጡት ሰዎች፣ እነዚያን በአላህ በመጨረሻዉ ቀን የማያምኑትን፣ አላህና መልክተኛዉ እርም ያደረጉትንም እርም የማያደርጉትንና እዉነተኛዉንም ሃይማኖት የማይቀበሉትን እነርሱ የተዋረዱ ሆነዉ ግብርን በእጆቻቸው እስከሚሰጡ ድረስ ተዋጉዋቸው።" (ሱረቱ-ተውባህ 29)።።

ይህንኑ አንቀጽ እንደተለመደው በመጥቀስ፡ ክርስቲያኖችን ግደሉ፡ ከገደላችሁ ትጸድቃላችሁ ይላል የሚል ክስ አቅርበዋል።።

ምላሽ፡-

1. ከላይ በተጠቀሰው አንቀጽ ውስጥ፡ የኩፍር አካላትን በተለይ የመጽሐፉን ሰዎች (አይሁድና ክርስቲያን) የምትጋደሏቸው እስኪሰልሙ ነው የሚል ጥቅስ አለ? እስኪ ያንን የሚያመላክት ኃይለ ቃል ከውስጡ ማውጣት ይቻላል? ለምን የሌለ ውሸት ይወራል?

2. በብዙ የቅዱስ ቁርአን አንቀጾች ላይ የመጽሐፉ ሰዎችን ወደ ኢስላም ጥሪ እንድናደርግላቸው ቅዱስ ቁርአን ይነግረንና፡ ከነሱ ግን የእንቢተኝነትን መልስ ብናገኝ፡ በአጸፋው ግደሏቸው ሳይሆን የሚለው፡ በሉ እንግዲያውስ እኛ ለአላህ እጅ የሰጠን ሙስሊሞች መሆናችንን መስክሩ፣ ብትመሩ ጥቅሙ ለናንተ ነው፡ እንቢ

ካላችሁም የመልክተኛው ግዳጅ መልክቱን ማድረስ ብቻ ነው ይላል፡፡ እስኪ ቀጣዮቹን አንቀጾች እንመልከታቸው፡-

قُلْ يَا أَهْلَ الْكِتَابِ تَعَالَوْا إِلَى كَلِمَةٍ سَوَاءٍ بَيْنَنَا وَبَيْنَكُمْ أَلَّا نَعْبُدَ إِلَّا اللَّهَ وَلَا نُشْرِكَ بِهِ شَيْئًا وَلَا يَتَّخِذَ بَعْضُنَا بَعْضًا أَرْبَابًا مِنْ دُونِ اللَّهِ فَإِنْ تَوَلَّوْا فَقُولُوا اشْهَدُوا بِأَنَّا مُسْلِمُونَ "سورة آل عمران 64

"የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! በኛና በናንተ መካከል ትክክል ወደሆነች ቃል ኑ፤ (እርሷም) አላህን እንጅ ሌላን ላንገዛ በርሱም ምንንም ላናጋራ፣ ከፊላችንም ከፊሉን ከአላህ ሌላ አማልክት አድርጐ ላይይዝ ነዉ፤ በላቸዉ። እምቢ ቢሉም ፡- እኛ ሙስሊሞች መሆናችንን መስክሩ በሏቸው" (ሱረቱ አሊ-ዒምራን 64)፡፡

ከዚህ አንቀጽ በግልጽ እንደምንረዳው፡- የመጽሐፉ ሰዎችን ወደ አንድ አምላክና አንድ አምልኮ ብቻ ወደ ሚፈጸምበት ኢስላም ጥሪ እንድናደርግላቸው ካዘዘን በኋላ፡ ነፍሱን ከጀሀነም ለማዳን ፈቅዶ የመጣ መልካም፡ እንቢ ብሎ በዛው ክህደቱ ወዘውተር የፈለገን ደግሞ፡ አስገድዱት፡ ወይም እስኪሰልም ድረስ ተጋደሉት ሳይሆን፡ እኛ ሙስሊሞች መሆናችንን መስክሩ በሏቸው ነው የሚለው፡፡

فَإِنْ حَاجُّوكَ فَقُلْ أَسْلَمْتُ وَجْهِيَ لِلَّهِ وَمَنِ اتَّبَعَنِ وَقُلْ لِلَّذِينَ أُوتُوا الْكِتَابَ وَالْأُمِّيِّينَ أَأَسْلَمْتُمْ فَإِنْ أَسْلَمُوا فَقَدِ اهْتَدَوْا وَإِنْ تَوَلَّوْا فَإِنَّمَا عَلَيْكَ الْبَلَاغُ وَاللَّهُ بَصِيرٌ بِالْعِبَادِ "سورة آل عمران 20

"ቢከራከሩህም :- ፊቴን ለአላህ ሰጠሁ፤ የተከተሉኝም ሰዎች (እንደዚሁ ለአላህ ሰጡ) በላቸዉ፤ ለእነዚያም መጽሐፍን ለተሰጡት ሰዎችና ለመሀይሞቹ፡- ሰለችማሁን? በላቸዉ፤ ቢሰልሙም በእርገጥ ተመሩ እምቢ ቢሉም በአንተ ላይ ያለበህ ማድረስ ብቻ ነዉ:: አላህም ባሮቹን ተመልካች ነው::" (ሱረቱ አሊ-ዒምራን 20)፡፡

ከዚህ አንቀጽም ተመሳሳይ ነገር እናገኛለን፡፡ በውስጡ ያለው መልክትም፡- ዐረብ መሃይማቹንና የመጽሐፉን ባለቤቶች ወደ ኢስላም እንዲመጡ ጥርሪ ማድረግ እንዳለብንና፡ ጥርሪውን ሰምተው ፈቅደው ከመጡ፡ በርግጥም ቅንን መንገድ ተመሩ፡ እንቢ ካሉ ደግሞ፡ ይገደሉ ሳይሆን፡ የናንተ ግዳጅ መልክቱን ማድረስ ብቻ ነው፡ ከዛም የባሮቼን ሁኔታ ተመልካች እኔ ነኝ ነው ያለው፡፡ ታዲያ የታለ በሃይማኖት ማስገደድ? የታለ ካልሰለሙ መግደል?

3. ከላይ ተጠቅሶ ወደነበረው አንቀጽ 29 ስንመለስ፡ እነዚህን አካላት ተጋደሏቸው ያለው እስከምን ድረስ እንደሆነ የአንቀጹ መቋጫ ላይ ገልጾታል፡፡ ቃሉም የሚለው ‹‹ግብርን በእጆቻቸው እስከሚሰጡ ድረስ ›› ነው እንጂ፡ እስኪሰልሙ ድረስ አይደለም፡፡ በኢስላማዊው ግዛት ውስጥ እስከኖሩ ድረስ ግብር መክፈል ግዳጃቸው ነው፡፡ የግብሩ ክፍያም ለነሱ፡ ሃይማኖታቸው ተጠብቆ እንዲቆይ፡ ደማቸው ያለ አግባብ እንዳይፈስ፡ ንብረታቸው በከንቱ እንዳይወረስ ከለላ ይሆናቸዋል፡፡

ወገኖች ሆይ! ዛሬ በሀገራችንም ሆነ በውጭው ዓለም ስትኖሩ ያለ ግብር (tax) ነው እንዴ የምትኖሩት? ለምን የእስልምናው ነገር ከበዳችሁ?

4. የግብር መክፈል ስርዓት እኮ ዛሬ በነቢዩ ሙሐመድ (ዐለይሂ-ሶላቱ ወስ-ሰላም) ሸሪዓ የተጀመረ አዲስ ነገር አይደለም፡፡ ከሳቸው በፊት በነበሩት ነቢያት ስርዓት ውስጥም የነበረ ነው፡፡ እንደውም በጣም የሚገርመው፡- የግብር አንቀጽ በቅዱስ ቁርአን ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ ሲጠቀስ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግን 31 ጊዜ ተጠቅሷል፡፡ ከነዚህ ውስጥ 22ቱ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሲሆን፡ የተቀረው ዘጠኙ ደግሞ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል ጥቂቶቹን እንመልከት፡-

ሀ. ከብሉይ ኪዳን፡-

"በጌዝርም የተቀመጡትን ከነዓናውያንን አላሳደዱአቸውም፥ እስከ ዛሬም ድረስ ከነዓናውያን በኤፍሬም መካከል ተቀምጠዋል፤ የጉልበት ግብርም ያስገብሩአቸው ነበር።" (መጽሐፈ ኢያሱ ምዕ 16፡ ቁ 10)፡፡

በዚህ ጥቅስ መሰረት፡ እስራኤላውያኖች በእግዚአብሄር ትእዛዝ ወደ ተቀደሰችዋ ምድር፡ ከእግዚአብሄር ሰው ከኢያሱ ጋር ሲገቡ፡ ከከነዓናውያን ግብርን በኃይል ተቀብለዋል፡፡ በተጨማሪ (መጽሐፈ መሳፍንት፡ ምዕ1፡ ቁ 26-30) ይመልከቱ፡፡

"ሰሎሞንም ከወንዙ ጀምሮ እስከ ግብጽ ዳርቻ እስከ ፍልስጥኤም ድረስ በመንግሥታት ሁሉ ላይ ነግሦ ነበር፤ ግብርም ያመጡለት ነበር፥ በዕድሜውም ሙሉ ለሰሎሞን ይገዙ ነበር።" (መጽሐፈ ነገስት ቀዳማዊ ምዕ 4፡ ቁ 21)፡፡

በዚህ ጥቅስም ላይ የዳዊት ልጅ ንጉስ ሰሎሞን (ነቢ ሱለይማን ዐለይሂ-ሰላም) ግብርን ይቀበል እንደነበር መረዳት ይቻላል፡፡

ግብር ለመክፈልና የዕርቅ ቃል ለመመለስ ፈቃደኛ ስላልሆኑ ህዝቦች ቅጣት ምን መሆን እንዳለበት እግዚአብሄር ሙሴን (ሙሳ ዐለይሂ ሰላም) እንዲህ ብሎ አዘዘው፡-

"ለመዋጋት ወደ አንዲት ከተማ በደረስህ ጊዜ አስቀድመህ በዕርቅ ቃል ጥራቸው። የዕርቅ ቃልም ቢመልሱልህ ደጅም ቢከፍቱልህ፥ በከተማ ውስጥ ያለው ሕዝብ ሁሉ ይገብሩልህ ያገልግሉህም። የዕርቅ ቃልም ባይመልሱልህ ከአንተም ጋር መዋጋት ቢወድዱ፥ አንተ ከተማይቱን ትከብባለህ ታስጨንቃትማለህ፤ አምላክህም እግዚአብሔር በእጅህ አሳልፎ በሰጣት ጊዜ፥ በእርስዋ ያሉትን ወንዶች ሁሉ በሰይፍ ስለት ትገድላቸዋለህ፤ ነገር ግን ሴቶቹንና ሕፃናትን እንስሶቹንም በከተማይቱም ያለውን ምርኮ ሁሉ በዝብዘህ ለአንተ ትወስዳለህ፤ አምላክህም እግዚአብሔር የሚሰጥህን የጠላቶችህን ምርኮ ትበላለህ። የእነዚህ አሕዛብ ከተሞች ባይደሉት ከአንተ እጅግ በራቁት ከተሞች ሁሉ እንዲሁ ታደርጋለህ።" (ኦሪት ዘዳግም ምዕ 20፡ ቁ 10-15)።

ይህ አንቀጽማ እንደውም ይገብሩልህ ብቻ ሳይሆን፡ በባርነት ስር አገልጋይ አድርገህ ሁሉ መያዝ ትችላለህ ነው የሚለው።

ዳዊትም (ዳዉድ ዐለይሂ-ሰላም) ግብር ማስከፈል ብቻ ሳይሆን እንዲህም ያደርግ ነበር ብሎ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል፡-

"ከዚህም በኋላ ዳዊት ፍልስጥኤማውያንን መታ፥ አዋረዳቸውም፤ ከፍልስጥኤማውያንም እጅ ሜቴግ አማ የተባለችውን ከተማ ወሰደ። ሞዓብን መታ፥ ሞዓባውያንንም በምድር ጥሎ በገመድ ሰፈራቸው፤ በሁለትም ገመድ ለሞት፥ በአንድም ገመድ ሙሉ ለሕይወት ሰፈራቸው፤ ሞዓባውያንም ለዳዊት ገባሮች ሆኑ፥ ግብርም አመጡለት።" (ሁለተኛ ሳሙኤል ምዕ 8፡ ቁ 1-2)።

ታዲያ ዳዊት ይህን ሁሉ ሲያደርግ ከስሜቱ ሳይሆን፡ በሄደበት ቦታ ሁሉ እግዚአብሄር ከሱ ጋር እንደነበረ ወደታች ወረድ ብሎ እንዲህ ይነግረናል፡-

"በኤዶምያስ ሁሉ ጭፍሮች አኖረ፥ ኤዶማውያንም ሁሉ ለዳዊት ገባሮች ሆኑ፤ እግዚአብሔርም ዳዊት በሚሄድበት ሁሉ ድልን ሰጠው።" (ሁለተኛ ሳሙኤል ምዕ 8፡ ቁ 14)።

ለ. ከአዲስ ኪዳን፡-

"ለሁሉ የሚገባውን አስረክቡ፤ ግብር ለሚገባው ግብርን፥ ቀረጥ ለሚገባው ቀረጥን፥ መፈራት ለሚገባው መፈራትን፥ ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ።" (ወደ ሮሜ ሰዎች ምዕ 13፡ ቁ 7)።

ጳውሎስ ግብር ለሚገባው ግብርን ክፈሉ፣ ለባለ ቀረጡ ደግሞ ቀረጥን ስጡ በማለት ለሮሜ ሰዎች መልክቱን ልኳል።።

"ኢየሱስም (ዒሳ ዐለይሂ-ሰላም) ግብር ከፋይ እንደነበር ማቴዎስ በወንጌሉ ላይ እንዲህ ጽፎታል፡-

ወደ ቅፍርናሆምም በመጡ ጊዜ ግብር የሚቀበሉ ሰዎች ወደ ጴጥሮስ ቀረቡና። መምህራችሁ ሁለቱን ዲናር አይገብርምን? አሉት። አዎን ይገብራል አለ...." (ማቴዎስ ወንጌል ምዕ 17፣ ቁ 24-25)።።

ከዚህ በኋላ አሁንም ኢስላምን ደግሞ ለመተቸት የሚችል አንደበት ይኖራቸዋልን?